| | |
|---|---|
| ዐይነት ፲ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፲ | "ፋሺዝም ፡ አልሞተም ። " |
| ደራሲ ፲ | አ..ሀ.ሥ.አ. ፥ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽ. ፡ ቤት ። |
| ዕለት ፲ | ነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፲ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፲ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-003 |
| ማስታወሻ ፲ | |
| ማሳሰቢያ ፲ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።
# Editorial | Éditorial

## ፋሺዝም ፡ አልሞተም ።

ሚያዝያ ፡ 27 ፡ አደባባይ ፡ እቆመው ፡ ያርበኞች ፡ መታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ተቀርጾ ፡ እንደምናነበው ፦

*"... ፡ ቢነገር ፣ ቢወራ ፥ ቢተረክ ፣ ቢጻፍ ፥*
*ፍጻሜ ፡ የለውም ፡ የፋሺስቶች ፡ ግፍ ። "*

ሲል ፡ ደራሲ ፡ የነገረው ፡ እውነት ፥ ከ 79 ፡ ዓመት ፡ በኋላም ፡ እውነትነቱ ፡ ሳያከትም ፥ ሕያው ፡ ምስክር ፡ ኾኖ ፥ ዘመናችንን ፡ የሚገልጽ ፡ ቃለ ፡ ምዕዳንን ፡ ያሰማል ።

ሕዝብን ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ከፋፍሎ ፡ የሚያባላ ፡ የስግብግብነት ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፥ እንደ ፡ አዶ ፡ ከበሬ ፡ ድንገት ፡ እየገዘፈ ፥ መርዶን ፡ በየቤቱ ፡ ሲያረዳ ፡ እንሆ ፡ 45 ፡ ዓመታት ፡ ዐለፉን ።

ዘንድሮ ፡ ደግሞ ፥ ፋሺዝም ፡ መልኩን ፡ ለውጦ ፥ ዐቅዳዊ ፡ ወገዳ ፡ በሚመስል ፡ ድርጊያ ፡ የገዛ ፡ ልጆቹን ፡ *"የክልል ፡ አመራር ፡ አባላቱን"* ፡ እና ፡ የጦር ፡ አበጋዞቹን ፡ እሚበላበት ፡ ረድፍ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፥ በሠኔ ፡ ወር ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ አሠቃቂ ፡ መጠፋፋትን ፡ አስፈጸመ ። ድርሱንም ፡ በዘር ፡ ማደራጃ ፡ ምክንያት ፡ አድርጎታል ።

የቀደሙት ፡ ትውልዶች ፡ የቀድሞውን ፡ ፋሺዝም ፡ በመሸሽ ፡ ወይ ፡ በመታገሥ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በማስታመም ፡ ድል ፡ አልነሡትም ። ምንነቱን ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፥ በመሥዋዕት ፡ ብቻ ፡ መሸነፉን ፡ ባስረገጡ ፡ ጊዜ ፥ ውዱን ፡ የሕይወት ፡ ዋጋ ፡ ከፍለው ፡ ድል ፡ ነሥተውታል ። የዛሬውን ፡ ፋሺዝም ፡ ከቀድሞው ፡ የሚለየው ፥ የኛኑ ፡ አካል ፡ ለብሶ ፡ መምጣቱ ፡ ነውና ፥ እያንዳንዳችን ፡ ራሳችንን ፡ ገዝተን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችንን ፡ በሥልጡንሕዝብናችን ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ በማጽናት ፥ ለዚህ ፡ ዲያብሎሳዊ ፡ የከፋፍለኽ ፡ ግዛ ፡ ኀይል ፡ መግቢያ ፡ ቀዳዳን ፡ ልናሳጣውና ፡ ድል ፡ ልንነሣው ፡ እንችላለን ። ይህም ፡ ሕዝባዊ ፡ እግዚእናን ፡ ማስከበር ፡ ይባላል ❖


©አ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።